# የ"ዞን 9 አባሎች"-- ጦማሪዎች ወይስ ህቡዕ ተቀጣሪዎች?

ቶሎሳ ኡርጌሳ Utolosa@yahoo.com

ትግራይ  ኦንላይን May 08, 2014

ከመሰንበቻው አንድ አሳዛኝና አሳፋሪ ክስተትን ሰምተናል። ይኸውም ራሳቸውን "**ዞን 9**" እያሉ የሚጠሩ ስድስት ግለሰቦችና ሶስት የግል "ጋዜጠኞች" ፌዴራል ፖሊስ 'በሰብዓዊ መብት ስም ከተጀቦኑ የውጭ ድርጅቶች ጋር በገንዘብና በሐሳብ ተስማምተው ሕዝቡን ለአመፅ ለማነሳሳት ሲንቀሳቀሱ ተደርሶባቸው' በማለት ጠርጥሯቸው በቁጥጥር ስር መዋላቸው ነው። ግለሰቦቹ በህጉ መሰረት የፍርድ ቤት የፍተሻ ወረቀት ቤታቸው ከተፈተሸ በኋላ በ48 ሰዓት ውስጥ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አራዳ ምድብ አንደኛ ወንጀል ችሎት ቀርበው ተጨማሪ የጊዜ ቀጠሮ ተጠይቆባቸዋል።

ይሁንና ከጉዳዩ ጀርባ ያሉና በሰብዓዊ መብቶች ስም ታጅለው ጥርሳቸውን በማሾል የሀገራችንን ሰላም፣ ልማትና የዴሞክራሲ ግንባታ ስርዓትን በቀለም አብዮት ለመቦጫጨቅ ታጥቀው የተነሱ "ድርጅቶች"፣ እንደ ፌስ ቡክ ያሉ ማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁም ጥቂት የዲያስፖራ ፅንፈኞች ሁኔታውን ወዳልተፈጠረበት አቅጣጫ ለመዘወር ሲሞክሩ ይታያሉ—ህዝቡን ለማደናገርና ተራ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት። በተለይም እንደ አርቲክል 19፣ ግብፅና ኤርትራ ያሉ የጉዳዩ ግንባር ቀደም ተዋናዮች በጦማሪዎቹና በግል "ጋዜጠኞቹ" መያዝ ምክንያት ተሸቀዳድመው "ምነው በአፈሩ ላይ…" እያሉ ደረታቸውን እየደቁ ሙሾ ሲያወርዱ አድምጠናቸዋል፤ሰምተናቸዋል።

እርግጥ የግብፅና የተላላኪው የኤርትራ መንግስት ፍላጎት ሀገራችን ውስጥ ስላምና መረጋጋት እንዳይኖር ቋሚ ሽብር መፍጠር መሆኑ ቢታወቅም፤ አርቲክል 19 ግን ለከፈለው ሁሉ የሚሰራ፣ ሴራ የሚጎነጉን ብሎም በተለያዩ ሀገራት ውስጥ ተላላኪዎችን በመፍጠር የቀለም አብዮት እየቀመረ በዴሞክራሲያዊ መንግስት የተመረጠን መንግስት ለመገልበጥ የተፈጠረ አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ኃይል መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው። በአጭሩ በበላበት የሚጮህ ውሻ ነው ልንለው እንችላለን።

እናም በቅድሚያ ራሳቸውን "ዞን 9" እንዲሁም የግል ጋዜጠኞች የነበሩትን ግለሰቦች ተጨባጭ ሁኔታን እኔ እንደሰማሁት ምን እንደሆነ ከመግለፄ በፊት፤ በእኔ እምነት "የጡት አባቶቻቸውን" እና ደጋፊዎቻቸውን ማንነት መመልከት አስፈላጊ ይመስለኛል። አባትን ማወቅ የልጅን ማንነት ለመገንዘብ ያስችላልና። ምክንያቱም እነ አርቲክል 19 በሌሎች ሀገራት ውስጥ ያካሄዱት የቀለም አብዮት ዘመቻና በእኛም ሀገር ውስጥ ለመከወን ያሰቡት ግና በእንጭጩ የተቀጨው ድርጊት ተመሳሳይ ስለሆነ ነው።

እርግጥ አክራሪው ኒዮ-ሊበራል ተቋም ምንም እንኳን በድረ-ገፁ ላይ በምስራቅ አፍሪካ ውስጥ የሚያከናውነውን ድርጊት አስመልክቶ “አርቲክል 19 ኢንፎርሜሽን የልማት ፖሊሲዎችና ክንዋኔዎቻቸው ገቢራዊ ይሆኑ ዘንድ ሚዲያና ዘመቻዎቹ በአብዝሃነትና በልዩነት እንዲሰሩ ለማረጋገጥ ይሰራል” በማለት ቢገልፀውም፤ ሃቁ ግን ይህ አይደለም። ለምን? ቢሉ፤ ድርጅቱ በየቦታው የቀለም አብዮት በማስነሳት የእነ ዲታው ጆርጅ ሶሮስን የኒዮ-ሊበራሊዝም ህልዮት ለማስፈፀም እንዲሁም አንድን ሀገር ለማጥቃት ሲል ከከፈለው ድርጅት ጋር ሁሉ የሚሞዳሞድ ስለሆነ ነው። እዚህ ላይ ሁለት አብነቶችን ማንሳት ይቻላል—እስከዛሬ ድረስ በቀለም አብዩት እየተናጠች ያለችውን ዩክሬይንን እና በሰላም፣ በልማትና በዴሞክራሲ ድንቅ ዕመርታ በማሳየት ላይ የምትገኘውን ኢትዮጵያን።

አርቲክል 19 በዩክሬይን የቀለም አብዮት የማቀጣጠል ተግባር ውስጥ ተዋናይ እንደነበር መረጃዎች ያመለክታሉ። ኒኮላይ ቦብኪን የተባሉ አሜሪካዊ የ“ስትራቴጂክ ሴንተር ፋውንዴሽን” ፀሐፊ እንደሚገልፁት፤ መቀመጫውን እንግሊዝ ያደረገው አርቲክል 19ኝን ጨምሮ በርካታ መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት ስም የሚንቀሳቀሱ መያዶች (NGO’s) የዩክሬንን ምሁራንና አክቲቪስቶችን ወደራሳቸው ተግባር በመሳብ ሴሚናሮችንና ውይይቶችን እያዘጋጁ በጣልቃ ገብነት የተለያዩ የሀገሪቱን መረጃዎች ሲሰበስቡ ነበር። በዚህም የሀገሪቱን የፖለቲካ ሁኔታ፣ ወታደራዊ አቅምን እንዲሁም ሃይማኖታዊና ማህበራዊ ኑባሬዎችን ልቅም አድርገው ከወሰዱ በኋላ፤ የተገኙ ዳታዎችን አሜሪካ ወደሚገኙት የኢንፎርሜሽን መተንተኛ ማዕከሎች እንደሚልኩ ያስረዳሉ።

በዚህ ስራ ውስጥ በቀለም አብዩት አቀጣጣይነታቸው የሚታወቁትና አስቀድመው እዚያች ሀገር ውስጥ የገቡት “ዝነኛዎቹ ደም አፋሳሽ” የውጭ መያዶች እነ አርቲክል 19፣ ናሽናል ዴሞክራቲክ ኢንስቲትዩት (NDI) ፣ ኢንተርናሽናል ሪፐብሊካን ኢንስቲትዮት (IRI) እና ናሽናል ኢንዶውመንት ፎር ዴሞክራሲ (NED) እንዲሳተፉ ይደረጋል። ዳታዎቹ ከተጠኑ በኋላም ዩክሬይን የሚገኘው የአሜሪካ ኤምባሲ የቀለም አብዩቱን ለማቀጣጠል ከውጭ ገንዘብ የማሰባሰብ ተግባሩን በንቃት ይወጣል።

ታዲያ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ‘ከዚህ በኋላ ምን ይፈጠራል?’ ብሎ መጠየቅ ያለበት አይመስለኝም። ምክንያቱም በእነዚህ የቀለም አብዩተኞች የተፈጠረውን የዩክሬይንን ውጥንቅጥ በሚገባ ስለሚያውቀው ነው። ዳሩ ግን የቀለም አብዩት ሞዴል ዩክሬይን ውስጥ ገቢራዊ ሳይሆንና የተፈለገውን ለውጥ እንዳላመጣ ምናልባትም አክራሪ ኒዩ-ሊበራሎቹ ትምህርት ያገኙበት ይመስለኛል—በቅርቡ የሀገሪቱ ፓርላማ “የውጭ ሰላዮች” ያላቸውን መያዶች የሚገዛ ህግ ማውጣቱን ተከትሎ ጦማሪዋ አን አፕልባም “ዩክሬይን የቀለም አብዮት ሞዴል መሞቱን ለዓለም አሳይታለች” እንዳለችው ማለቴ ነው።

ያም ሆነ ይህ ግን እነ አርቲክል 19 በዩክሬይን ውስጥ የሀገር ፍቅር የሌላቸውንና ራሳቸው ጠፍጥፈው የሰሯቸውን "ጦማሪዎችን"፣ የግል ጋዜጠኞችን እንዲሁም አንዳንድ የሀገር ውስጥ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ከማሰለፍና ለቀለም አብዮት እንዲያሰፈስፉ ከማድረግ አልቦዘኑም። እንዲያውም ተቋሙ ዩክሬይን ውስጥ ካለቀው የሀገሪቱ ዜጋ ይልቅ የእርሱንና አጋሮቹን ተግባር አንግበው የራሳቸውን ህዝብ በመረጃ ሲያደናግሩ እንዲሁም ዛሬ ወደ ሩሲያ የተቀላቀለችው ክሬሚያ እንዳትገነጠል በማህበራዊ ሚዲያዎች የሞት ሽረት ትግል ሲያደርጉ የነበሩትን ግለሰቦች እንዲለቀቁ ዓይኑን በጨው ታጥቦ ሲጠይቅ ነበር። ከእነዚህም ውስጥ የግል ጋዜጠኞችና አክቲቪስቶች እንዲሁም ጦማሪዎችና ፎቶግራፈሮች የሆኑት አሌክሲ ግሪስንኮ፣ ሰርጌር ሱፐረን፣ ናታልያ ሉካያንቼንኮ፣ አንድሪ ሼኩን፣ አንቶኒ ኮቫልስኪ፣ ኤሊና ማክሲሜንኮ፣ ኦሌስ ክሮምፕላስ፣ አሌክሳንድራ ራያዛንትስቫ እና ካትሪያና ቡትኮንን መጥቀስ ይቻላል።

ይህ ሁነትም ዩክሬይን ውስጥ የነበረችው የክሬሚያ ግዛት ውስጥ ያሉ ህዝቦች ከሩሲያ ጋር ለመቀላቀል አሊያም ከዩክሬይን ጋር ለመቀጠል እንደ ነገ ህዝበ-ውሳኔያቸውን በድምፅ ለመግለፅ በተዘጋጁበት ወቅት የተከናወነ በመሆኑ፤ አርቲክል 19 ተግባሩ በምንም መልኩ እርሱ በድረ ገፁ ላይ "ለጋዜጠኞች የስራ ነፃነት ቆሜያለው" ከሚለው ልቦለዳዊ ድርሰቱ ጋር የሚገናኝ አለመሆኑን በገሃድ የሚያሳይ ነው። ታዲያ እዚህ ላይ የእነ አርቲክል 19 ነገር በሰው ልጆች ደም የሚጋገር የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች "የዕለት እንጀራ" ጉዳይ ነውና 'እነዚህ ሃይሎች ለምን እንዲህ ያደርጋሉ?' ማለት የሚቻል አይመስለኝም። ምክንያቱም የሆድ ነገር ሆድ ስለሚቆርጥ እንዲሁም እነርሱ ለሌላው ሀገር ዜጎች የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል ርህራዬ ስለሌላቸው ነው።

እንደ እውነቱ ከሆነ የቀለም አብዮት ባህሪ ምናልባትም የድርጊቱ ፈጣሪዎች ከየሀገራቱ ነባራዊ ሁኔታ አንፃር የሚለያዩት ካልሆነ በስተቀር፤ ጥቅል አፈፃፀሙ አንድ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህም ከሀገራችን አኳያ እነ አርቲክል 19 የሀገራችንን የመጪውን ዓመት ምርጫ ተከትሎ ለቀለም አብዮት መደላድል ለመፍጠር ያደረጉትን ሙከራ መጥቀሱ በቂ ይመስለኛል። እንደሚታወቀው አርቲክል 19 እና መሰል አክራሪ ኒዮ-ሊበራል ሃይሎች የሀገራችንን ሁለንተናዊ ዕድገት የኋሊት ለመቀልበስ ያልሞከሩት ሴራ የለም። ከሪፖርት ጋጋታ እስከ የቀለም አብዮት ጋሻ ጃግሬዎችን እስከ መመልመል ድረስ ተፍጨርጭረዋል፤ ምናባዊና ተግባራዊ ዳገት ወጥተዋል፤ ቁልቁለት ወርደዋል። የጉዟቸው ልኬት ትክክል ይሁን አሊያም የተሳሳተ በትክክል መመዘን አልቻሉም እንጂ።

አርቲክል 19 በሌላው ሀገር ውስጥ እንደሚያካሂደው ሁሉ፤ ሀገራችንም ውስጥ በማህበራዊ ሚዲያዎች ህዝቡን በመረጃ ለማደናገር በቅድሚያ ያከናወነው ድርጊት የግል "ጋዜጠኞችን" (በተለይም በመንግስት

ላይ ጥላቻ ያላቸውን በማስጠናት) ለስልጠና ወደ ናይሮቢ መጥራት ነበር። እኔ እንደሰማሁት በአሁኑ ወቅት ዕውቅና የሌለውና በአስገራሚ ሁኔታ ‘መንግስት ዕውቅና ካልሰጠኝ እንደ ህጋዊ አካል ራሴን ቆጥሬ ስራዬን እቀጥላለሁ’ በማለት ከወዲሁ ህገ-ወጥነትን የሚያቀነቅነው፣ የተላከበትን የጉዳይ አስፈፃሚነት ተልዕኮን ለማሳካት ደፋ ቀና የሚለውና ራሱን የኢትዮጵያ ጋዜጠኞች መድረክ (ኢጋመ) እያለ የሚጠራው ስብስብ የቀለም አብዮት አበጣባጭነት “ስጋ- ወደሙን” ቁርባን ወስዶ ተመልሷል። ከመሰንበቻው በፖሊስ ተጠርጥረው ፍርድ ቤት የቀረቡት 9 ግለሰቦችም በድብቅ በየሆቴሉ ውስጥ  በአርቲክል 19 በድብቅ ስልጠና ሲሰጣቸው እንደነበር ሰምቻለሁ።

ይህን ዕውነታ ሚዛን እንዲደፋ የሚያደርገው ሌላው ጉዳይ አንድ የአርቲክል 19 አባል ወደ ሀገራችን በመምጣት እነዚሁን ጦማሪዎችና የግል “ጋዜጠኞች” እንዲሁም ዕውቅና አልቦውን “ማህበር” ስብስብን ‘ለማሰልጠን ነው’ በሚል ሽፋን የተለያዩ ዶክመንቶችን ይዘው ሲገቡ በፀጥታ ሃይሎች ቁጥጥር ስር ከዋሉ በኋላ፣ ከቦሌ አለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እንዲመለሱ የመደረጋቸው ትዕይንት ነው። የተቋሙ ተመራማሪ መሆናቸውን የሚናገሩት ኬንያዊው ፓትሪክ ሙታይ ምንም እንኳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክንያት “ለሁለት ቀናት በደብረዘይት ከተማ ይካሄድ ለነበረ ስልጠና ለመስጠት ነው” በማለት ቢናገሩም፤ ሰውዬውም ሆኑ ስልጠና የሚሰጣቸው አካላት ምንም ዓይነት ፈቃድና ህጋዊ ዕውቅና የሌላቸው ናቸው። ከሁሉም በላይ ግን እጅግ አስቂኙ ነገር ሰውዬው “ለስልጠናው” ይዘውት የመጡት ዶክመንቶች ናቸው። ከዶክመንቶቹ ውስጥም ሁሉም ማለት ይቻላል ስለ “Safety & security” (ጥንቃቄና ደህንነት) የሚያትቱ ናቸው።

እርግጥ የዚህ ፅሑፍ አንባቢ ‘የጥንቃቄና ደህንነት ስልጠና እኛ ሀገር ውስጥ ምን ይሰራል?’ የሚል ጥያቄ ሊያነሳ ይችላል። አዎ! ጥያቄው ትክክል ነው። ለምን? ቢሉ፤ ሀገራችን ውስጥ አስተማማኝ ሰላም ያለ በመሆኑ ነው። በአስተማማኝ የሰላም ዓውድ ውስጥ ጋዜጠኛም ሆነ ማንኛውም ግለሰብ ደህንነቱን በጥንቃቄ መጠበቅ እንዳለበት የሚታወቅ ቢሆንም፤ ከሙያ አንፃር ጊዜ፣ ወቅትና ቦታ ተመርጦለት እንዲሁም የውጭ በጀት ተመድቦለት ሊካሄድ አይችልም—ኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ በኩል የሚያስጋ ምንም ዓይነት ነገር የለምና። እናም ስልጠናው መሰጠት ያለበት አል-ሸባብ በተቆጣጠራቸው ሰላም አልባ ጥቂት ቦታዎች አሊያም አፍጋኒስታን ወይም ኢራቅ ውስጥ እንጂ እኛ ሀገር ሊሆን አይደለም—ጋዜጠኞች ሙትና ቁስለኛ እየሆኑ ካሉባቸው ሀገራት ውስጥ የሚመደቡት ናቸውና። በመሆኑም እነዚህ ሀገራት ውስጥ ለሚሰሩ “ጋዜጠኞች” እና ጦማሪዎች “የጥንቃቄና ደህንነት” ስልጠና መስጠቱ አግባብነት አለው። እንደ እውነቱ ከሆነ አርቲክል 19 በትክክል ለጋዜጠኞች ሙብት የቆመ ቢሆን ኖሮ እኛ ሀገር ውስጥ መስጠት ያለበት ስልጠና “Peace Journalism” (የሰላም ጋዜጠኝነት) መሆን በተገባው ነበር። እናም በሌላ ነባራዊ

ሁኔታ የ“ጥንቃቄና ደህንነት” ስልጠናን በግድ ጎትቶ  ወደ እኛ ሀገር ለማምጣት መሞከር “አያ ጅቦ ሳታመሃኝ ብላኝ” ማለት ከመሆን የዘለለ ምንም ትርጉም የሚሰጥ አይደለም፡፡

ዳሩ ግን በእኔ እምነት አርቲክል 19 ይህን ስልጠና ለመስጠት የፈለገበት ዋነኛው ምክንያት ግልፅ ነው፡፡ ይኸውም ተቋሙ በተሳሳተ ስሌት የቀጠራቸው ተጠርጣሪ ጦማሪዎችና “ጋዜጠኞች” እንዲሁም ዕውቅና አልባው የጽንፈኛ ጋዜጠኞች ስብስብ እንዲያከናውኑ የሰጣቸው ተግባር ህገ-ወጥና ህዝብን ለብጥብጥ የሚዳርግ መሆኑን ስለሚያውቅ ለእነርሱ ሽፋን ማበጀቱ ነው፡፡ ካለው የቀለም አብዮትኝነት ብሎም በጎዳና ላይ ነውጥ ንፁሃንን አስገዳይነት ልምዱና ተሞክሮው በመነሳት አስቀድሞ የመከላከል ስልት መዘየዱ ነው ሊባልም ይችላል፡፡ ይሁንና የህግ የበላይነት በሰፈነበት ሀገር ውስጥ ጋዜጠኛም ይሁን ዜመኛ፣ ተኳሽም ይሁን ቀዳሽ፣ ጦማሪም ይሁን ዘማሪ…ሁሉም ዜጋ ህግና ስርዓትን አክብረው ሊሰሩ የግድ እንደሚላቸው ድርጅቱ ሊያውቅ ይገባል—በየትኛውም ሀገር የሚገነባ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሁለት እግሩ ቆሞ እየፈካና እያበበ ሊሄድ የሚችለው የህግ የበላይነት ሲረጋገጥ ብቻ ነውና፡፡

እናም ተቋሙ ያሰበው የብጥብጥ ሴራና ኋላ ላይም ተጠርጣሪ ግለሰቦችን ለማዳን ያለመበት የ“ጥንቃቄና ደህንነት” ስልጠና በምድረ-በዳ ላይ እንደተዘራ ዘር መቁጠር ይኖርበታል ባይ ነኝ— እያንኳኳ ያለው የተሳሳተን በር ነውና፡፡ የተሳሳተ በርን የሚያንኳኳ ማንኛውም ግለሰብ ይሁን ቡድን ደግሞ ዘው ብሎ የሚገባው የሌላ ሰው ቤት በመሆኑ፤ ቢያንስ በሀገራችን የውስጥ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ በሚፈተፍተው ጣልቃ ገብነቱ ሊያፍር፣ ከፍ ሲልም “በኢትዮጵያ በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት 9 ጦማሪዎችና የግል “ጋዜጠኞች” ሃሳባቸውን በነፃነት ስለገለፁ የታሰሩ በመሆናቸው በአስቸኳይ እንዲፈቱ እንጠይቃለን” ከሚለው የቁራ ጩኸቱ ሊታቀብ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እንደ ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ የሚጮህበት የአክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች የከሸፈ ስልት “የተበላ ዕቁብ” መሆኑን ማንኛውም ዜጋ በቀላሉ ስለሚገነዘበው ነው፡፡

ታዲያ እዚህ ላይ ቀደም ሲል በይደር ያቆየሁትን “የዞን ዘጠኝ አባሎች—ጦማሪዎች ወይስ ህቡዕ ተቀጣሪዎች?” የሚለውን ጥያቄ ማንሳት ያስፈልጋል፡፡ ‘ዕውን አርቲክል 19 እና መሰል አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች እንደሚሉት ሀገራችን ውስጥ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት ስለሌለ ይሆን ጦማሪዎቹና የግል “ጋዜጠኞቹ” ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር የዋሉት?’ የሚለውንም ጥያቄያዊ አመክንዩ እንዲሁ መሳ ለመሳ ማየት ይገባል፡፡…እርግጥ ኢትዮጵያ የመደራጀት፣ የመሰብሰብ፣ ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ ወዘተ…መብቶችን በህገ-መንግስቷ ላይ በግልፅ ከመደንገጓም በላይ፣ ገቢራዊ ካደረገቻቸው 23 ዓመታት ማስቆጠሯን ለዚህ ፅሑፍ አንባቢ መንገር “ለቀባሪው የማርዳት” ያህል ይቆጠርብኛል፡፡ ምክንያቱም ዛሬ ላይ ሀገራችን ውስጥ ከ36 በላይ መፅሔቶችና ጋዜጦች ለህትመት የሚበቁበት፣ ፅንፈኛ ፖለቲከኞች ሳይቀሩ ‘ውልደቴ፣ ፖለቲካዬ፣ ብሶቴ፣ መኢሶንነቴ፣ ድንጉላነቴ፣ ዕድገቴ፣ ዕርገቴ፣ ምጥቀቴ፣ ምንቴቴ…’ እያሉ የባጥ የቆጡን

እንዳሻቸው የሚለፍፉባቸው መፅሐፎች ያለ ከልካይ እየታተሙ ለህዝብ የሚሰራጩበት፣ በርካታ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች በሰላማዊ ሰልፍ የፈለጉትን የሚናገሩበት ምህዳር መኖሩ የአደባባይ ምስጢር ስለሆነ ነው።

ከመገናኛ ብዙሃኑ ውስጥ ጥቂት የርዕስ ሰበዞችን መዘን ብንወስድ እንኳን "የፋክቱ" ፅንፈኛ እንደ አቶ ተመስገን ደሳለኝ "ለፍትህ ስርዓቱ ሲባል ስርዓቱ ይፍረስ፣ የፈራ ይመለስ፣ ለምን ትፈራለህ...ወዘተርፈ" የሚሉና ሌሎች ከሀገሪቱ ህግ ጋር የሚቃረኑ አመፅ ቀስቃሽ ፅሑፎች ይስተናገዳሉ። በአንድ ወቅት "ኢህአፓዎች አስቸገሩን። ምን እናድርግ?" ተብለው በአምባገነኑ ሌተና ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ምክር ተጠይቀው፣ "እኛን ምን አድረጉ ትሉናላችሁ! መሳሪያው ያለው እናንተ ጋር አይደለም እንዴ?" በሚል ጥያቄን በጥያቄ የሚመልስ፣ ነገር ግን "በለው!" በሚል ሰቅጣጭ ምላሽ መስጠታቸው የሚነገርላቸው ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም እንኳን ሳይቀሩ፤ ዛሬ በስተእርጅና እና ደጀ ሰላም በመቆሚያ ጊዜያቸው ከመሬት ተነስተው የህዝብ ተቆርቋሪ በመምሰል ከሚፅፏቸው "አናቄሬ" መጣጥፎች ባሻገር፣ የተለያዩ ነውጥን ያነገቡ መፅሐፎችን በገሃድ እየቸበቸቡ ያሉባት ሀገር ናት—ኢትዮጵያ። ይህን ነፃነት የሰጣቸውን ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ሳይቀር በአንድ ወቅት "ህገ-አራዊት" ማለታቸውን ሳንዘነጋ ማለቴ ነው።

እኔ እንደምገነዘበውም እንደ የኛ ፕሬስ ዓይነት ጋዜጦች በህዳሴው ግድብ ዙሪያ ከሀገራቸው ብሔራዊ ጥቅም ተፃራሪ በሆነ መንገድ የእነ ግብፅን አቋም እንዳሻቸው የሚያንሸራሽሩባት እንዲሁም በምርጫ 97 ወቅት የጎዳና ላይ አመፅ በማቀጣጠል የሚታወቁና በህግ የተዘጉ ጋዜጦችን አምዶች በማሰባሰብ ከአስር ዓመት በኋላ "በአዲስ መልክ ልንነውጥ መጥተናል" ብለው በገሃድ የሚናገሩ አፍሮ ታይምሶችም የሚስተናገዱባት ሀገር ናት—ኢትዮጵያ። ታዲያ እነዚህ የህትመት ውጤቶች ዕውቅና የተሰጣቸው በሀገራችን የብሮድካስት ባለስልጣን እንጂ በውሸት ዶላችው አርቲክል 19 አለመሆኑንም እዚህ ላይ ልብ ማለት ይገባል። ይህ ሃቅም የሀገራችን ልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንገስት ሃሳብን በነፃነት ለመግለፅ ዴሞክራሲያዊ መብት ምን ያህል ዕውቅና የሚሰጥና ለገቢራዊነቱም የሚተጋ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

እናም እንዲህ ዓይነቶቹ ከሀገራችን ህጎች ጋር የሚቃረኑ ተግባራት በሚዲያ ስም በሚፈፀሙባት ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ፤ ጦማሪዎቹና የግል "ጋዜጠኞቹ" ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን ተጠቅመው ሃሳባቸውን በነፃነት በመግለፃቸው ለእስር ተዳርገዋል የሚለው መራር ቀልድ የሚያስቅ አይደለም—የሚያሳዝንና የሚያስተዛዝብ እንጂ። ፖሊስም ራሳቸው በድረ-ገፃቸው ላይ "ያልተደራጀንና ዕውቅና የሌለን ነን" ሲሉ የመሰከሩ በህቡዕ ተግባራቸው የጠረጠራቸውን ግለሰቦች ካለበት የህግ የበላይነትን የማስጠበቅ

ሃላፊነት አኳያ ህግ ፊት ማቅረቡ ክፋቱ ምን እንደሆነ ለማንም ግልፅ ሊሆን አይችልም—ከበሬ ወለደ ድርሰት መግለጫ አውጪዎችና ተባባሪዎቻቸው በስተቀር።

ያም ሆነ ይህ ግን ለማንኛውም የሚዲያ ባለሙያ ፈቃድ በሚሰጥበት ሀገር ውስጥ፣ ተጠርጣሪዎቹ ጦማሪዎችና የግል "ጋዜጠኞች" ለምን ተግባራቸውን በህቡዕ መከወን ፈለጉ?፣ ሃሳብን የመግለፅ የዴሞክራሲ ብርሃን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየደመቀ በሚሄድባት ሀገር ውስጥ ለምን በጨለማ ውስጥ መሸሸግን መረጡ?፣ ለምንስ በጨለማ ውስጥ ሆነው ብርሃንን ለማየት አፈሩ?...እርግጥም "ምን ያለበት ዝላይ አይችልም" እንዲሉ፤ ዕውነታውን ለማወቅ የግድ ነብይ አሊያም ጥልቅ ተመራማሪ መሆን አይገባም። ነገርዬው ገሃድ ነውና። እውነትም ሃቁ እነዚህ ተጠርጣሪዎች 'ሲያከናውኑ ነበሩ' የተባሉበትን ምክንያት ሚዛን የሚደፋ ነው። ምክንያቱም ተጠርጣሪዎቹ "የጨለማው ዘማሪዎች" በታሰሩበት ማግስት የሰማሁትንና 'ግለሰቦቹ በህቡዕ በመደራጀት ሀገራችን ውስጥ የቀለም አብዮትን ያለ ቦታው ለመፍጠር ከሚታትረው አርቲክል 19 እና መሰሎቹ ጋር የሐሳብ ጋብቻ ፈጥረዋል፤ ከኤርትራና ከግብፅ መንግስታትም ገንዘብ ተቀብለዋል' የሚለውን ዕውነታ እንድቀበል ስለሚያስገድደኝ ነው። ለነገሩ ተግባራቸው ህገ-ወጥ፣ ህዝብና ሀገርን የሚጎዳ በተለይም የግብፅ ጉዳይ አስፈፃሚ የሆነው የኤርትራን መንግስት ፀረ-ኢትዮጵያ የትርምስ አጀንዳን የያዘ መሆኑን ስለሚያውቁ ድርጊታቸውን ከብርሃን ሰውረው እንደ ጅብ በጨለማ መከወናቸውን አሳምረው ስለሚያውቁት መደበቃቸው አይገርምም።

ይሁንና ሁኔታውን እንደ ዜጋ ስንመለከተው አሳፋሪው ነገር፣ ትናንት "አዲስ አበባን እንደ ባግዳድ እናደርጋታለን" ያለውንና ይህ ቀቢፀ-ተስፋው እንደ ጉም ብን ብሎ የጠፋውን የሻዕቢያን ህልም ለማሳካት እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝብ የዘመናት ቁጭት የሆነውን፣ የ'አይቻልም'ን መንፈስ የሰበረውንና እንደ ዓይኑ ብሌን የሚመለከተውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ በሁከት እንዲቋረጥ ባንዳ ሆኖ መሰለፍ ነው። አባቴ ይሙት! ማንኛውም ዜጋ በእነርሱ ቦታ ሆኖ ማፈሩ አይቀርም። ባንዳነት ሀገራችን ውስጥ 'ወንዜነት' የሌለው ሀገርን አሳልፎ የመስጠት አሳፋሪ እሳቤ ነውና።

እርግጥም ለገንዘብ ሲባል አዲስ አበባን የዩክሬይኗ ኪዬቭ ለማድረግ ከእነ አርቲክል 19፣ ከኤርትራና ከግብፅ ጋር ሀገርን ሸጦ መሞዳሞድ ታሪክ ይቅር የማይለው ሐጢያት ይመስለኛል። እንደ እውነቱ ከሆነ ማንኛውም ዜጋ በቀለም አብዮት እስካሁን ድረስ ፍዳዋን እያየች ያለችውን ዩክሬይንን ዕጣ- ፈንታ የሀገራችን ህዝብ እንዲገጥመው የሚሻ አይመስለኝም። ምክንያቱም ያቺ ሀገር በቀለም አብዮት ቋያ እሳት ዛሬም ድረስ እየተለበለበች ስትሆን፣ ወላፈኑን ደግሞ እንደ አርቲክል 19 ያሉ አክራሪ ኒዮ-ሊበራሎች በርቀት እየሞቁት ስለሆነ ነው። በሰው ሀገር ውስጥ ጣልቃ ገብተው የራሳቸውን ቀይ መስመር ካሰመሩና የንፁሃን ቀይ ደም እንዲፈስ ካደረጉ በኋላ በዚያች ሀገር ምስቅልቅል መሆን እየተዝናኑ ቀይ ወይናቸውን

እየተጎነጩ በሳቅ ዓለም ውስጥ እየዋኙ በመሆናቸው ነው። ሰውነታቸውን ሰድደውና ከሰብዓዊነት ወጥተው የማንንም ህልፈተ-ህይወት ከመጤፍ ሳይቆጥሩ በሰው ቁስል ውሰጥ እንጨት እየዶሉ “የዕለት ዳቦአቸውን” እየጋገሩ ስለሆነ ነው። እኔ እስከሚገባኝ ድረስ ግን የእነዚህን የፅንፈኛ ኒዮ-ሊበራሎችንና የኢትዮጵያ ጠላቶችን እኩይ ምግባር ለሽርፍራፊ ሳንቲም ሲል አንግቦ የህዝቡን ሰላም ለመሸጥ የሚቋምጥ ወገን ህሊናው የታወረ ነው። እናም ዜጋውን ለገንዘብ ሲል ለህልፈት ለመዳረግ ጨለማ ውስጥ ሆኖ በአደባባይ የሚቆምር ኢትዮጵያዊ/ት እርሱ/ሷ የመፅሐፍ ቅዱሱን የነብር ዥንጉርጉርነት የማይቀየርበትን ተምሳሌትነት የሻረ/ች ነውና/ናትና ከእኛ እንደ አንዱ ሊሆን/ልትሆን አይችልም/አትችልም። እናም እኔም ፍርዱን ለሚዛናዊው ለሀገሬ ህዝብና የጉዳዩ ባለቤት ለሆነው ፍትሐዊው የፍትህ ስርዓት በመተው ፅሑፌን በዚሁ እቋጫለሁ።